# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

## የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚዲቅሳ መፈታትን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የፓርቲያችን ሊቀ መንበር ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ታህሳስ 20/2001 ዓ.ም ዳግም መታሰርዋን ተከትሎ ለሃያ ወራት ያክል በእስር ከቆየች በኋላ ትናንት መስከረም 26/2003 ዓ.ም ከእስር ተፈታለች፡፡ በዚህ አጋጣሚ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ አባላትና እና ደጋፊዎች በወ/ሪት ብርቱካን መፈታት ታላቅ ደስታና እፎይታ የተሰማቸውን መሆኑን ለመግለጽ ይወዳሉ፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን፤ልጇ ሃሌና አዛውንት እናቷ ወ/ሮ አልማዝንም እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ለዚህ አበቃችሁ ይላቸዋል፡፡

ብርቱካን ለዳግም እስር ከተዳረገችበት ቀን ጀምሮ እርምጃውን በመቃወም "ብርቱካን ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ትፈታ" በማለት ለጮሃችሁና ለታገላችሁ፣ ኢትዮጵያውያን፤ ቁርና ድካም ሳይበግራችሁ በየአደባባዩ "ብርቱካን ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ትፈታ" ብላችሁ ለታገላችሁ በሰላ ብዕራችሁና አንደበታችሁ የብርቱካንን እስር አላግባብነት ተቃውማችሁ ተፈታ ዘንድ በአለም አቀፍ የሚድያ መድረኮች ለተሟገታችሁ ኢትዮጵያውያትና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ ያላችሁ እያልን ወደፊትም በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ የደረሰውን  በገዛ ራሳችሁ እንደደረሰ በደል በመቁጠር ሌሎች የሕሊና እስረኛ ኢትዮጵያውያን እንዲፈቱ በጋራ እንደምትቆሙ ሙሉ እምነት አለን፡፡

የኢህአዴግ መንግስት ወ/ሪት ብርቱካንን  ዳግም ማሰሩና አላግባብ በእስር ላይ ማቀየቱ አላግባብ ቢሆንም በመፍታት የወሰደውን እርምጃ ፓርቲያችን እንደ በጎ ጅምር ይመለከተዋል፡፡ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ችግር ሊፈታ የሚችለው በጉልበትና በእልህ ሳይሆን በመግባባትና በመደራደር መሆኑን ተገንዝቦ ለእንደዚህ ዓይነቱ በጎ እርምጃዎች ከልብ እንዲተጋም ፓርቲያችን ይጠይቃል፡፡ የአንድነት ፓርቲ ወ/ት ብርቱካን ትፈታ ዘንድ የተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ለአደረጉት ጥረት አክበሮቱን ይገለፃል፡፡

የወ/ሪት ብርቱካን እስር አግባብ አለመሆኑን ተገንዝበው የኅሊና እስረኛ መሆንዋን በግልጽ ከማወጅ አልፈው ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንድትፈታ ለወተወቱና በጎ ተጽእኖ ላሳረፉ ዓለም አቀፍ ተቋማትና መንግስታት አንድነት ፓርቲ ያለውን አክብሮት መግለጽ ይወዳል፡፡

አንድነት ፓርቲ ወ/ሪት ብርቱካን ይቅርታ ጠይቃ መፈታትዋን ግንዛቤ ወስዶአል፡፡ እንደ ፓርቲያችን ሊቀመንበርነቷ ወ/ሪት ብርቱካን በፓርቲው ፕሮግራምና መርሕም ይሁን በፓርቲው ሕገ ደንብ ያደረሰችው ጉዳትም ሆነ በደል እንደሌለ አንድነት ያምናል፡፡ በአገር ጥቅምና ሉአላዊነት የማትደራደር ፖለቲከኛ እንደሆነች የአገርን ሃብት በመመዘበርም የማትጠረጠር  እንደሆነች ፓርቲዋ አንድነት ጽኑ እምነት አለው፡፡ በመሆኑም አንድነት

በአንድ በኩል ይቅርታ የጠየቀችበትን የግል ውሳኔ እንደሚያከብር እየገለጸ በእስር ይዞ ያለችውን እንድትል የጠየቃት መንግስት ከእርሷ ይህን ለመጠየቅ የሞራል ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡

ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተቃዋሚዎች ላይ ተስፋ እንዲቆርጥና ለተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ያለውን ክብር እንዲቀንስ ከፍተኛ የስነ ልቦና ዘመቻ በማካሄድ ላይ እንዳለ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይገነዘባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "ያለ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ አንድነት አይዘልቅም" እስከማለት ድረስ የዘለቀ ከእኛ ወዲያ ላሳር የሚል ራስን የመካብ ዘመቻ እያካሄደ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ይህች አገር አንድና አንድ ሰው ብቻ ያላት እስኪመስል ድረስ ኢህአዴግ የገዘራሱን ሊቀ መንበር ተክለሰውነት (Personality cult) ለመገንባት እያደረገ ያለው ጥረትም ይታወቃል፡፡

ወ/ሪት ብርቱካን ይቅርታ ጠየቀየች መባሉ አልበቃ ብሎ እነዚያ በመንግስት የተገለጹት ሐረጎች የተፈለጉትም ለዚህ አላማ እንደሆነና ወደፊትም የጠንካራ ተቃዋሚ መሪዎችን ክብር ዝቅ ለማድረግ ያስችላል ያለውን ማንኛውንም ስልት ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይል አንድነት ይገነዘባል፡፡ እውነቱን ለሚያውቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዚህ ያለውን የወረደ የኢህአዴግ አስተሳሰብ ገዝቶ ለብርቱካን ያለውን ከበሬታ ከመቀነስ ይልቅ ለዚህ መንግስት ያለውን ግምት ይበልጡ ዝቅ እንዲል ያደርገዋል ብለን እናምናለን፡፡ በዚህ የኢህአዴግ ስልት ተነድቶ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ መድረስ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ሰፈር ጠንካራና ተአማኒ መሪዎች እንዳይኖሩት የማድረግ የኢህአዴግ ስትራቴጂ ሰለባ መሆን እደሆነ ልናስገነዝብ እንወዳለን፡፡

በመጨረሻም ፓርቲያችን አንድነት ሌሎች የህሊና እስረኞችም እንዲፈቱና በሕገ መንግሥቱ የሰፈሩት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ የሚያካሂደውን ሠላማዊ ትግል አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

መስከረም 27/2003 ዓም

አዲስ አበባ